# የACPS - የ2024-25 የበጎ-ፈቃደኝነት ስራ/Volunteer የመመሪያ-መጽሐፍ (Handbook)



# አጠቃላይ-ዕይታ

የአሌክሳንድሪያ ከተማ የሕዝብ ትምህርት ቤቶች (Alexandria City Public Schools (ACPS) - የሁሉንም የበጎ-ፈቃደኝነት ሠራተኞቻችንን - ትጋት እና አስተዋጾዖዎችን - ጥልቅ-የሆነ ዋጋ የምንሰጠው ነው። በACPS ትምህርት ቤቶች እና ተቋሞች ውስጥ፣ በበጎ ፈቃደኝነት ለመስራት የሚፈልግ ማንኛውም-ሰው፣ በኦንላይን ላይ የACPS የበጎ-ፈቃደኝነት ማመልከቻን በማስገባት፣ እና የACPSን የስነ-ምግባር ደንብ (Code of Conduct)ን እና የሚጠበቁ-ነገሮች - ላይ በመፈረም፤ በመጀመሪያ ፈቃድ-ማግኘት አለበት። ክፍላች/divisionን፤ የወንጀለኛነት እና የወሲብ-ጥቃት ወንጀለኝነት የቀደመ-ታሪክ መኖርና-አለመኖሩን ለማየት - ለእያንዳንዱ ማመልከታ፣ የ'Raptor Volunteer Management system'ን ይጠቀማል። እንደ የበጎ-ፈቃደኛ ሠራተኛ ለመሆን የሶሻል-ሴኩሪቲ (Social Security) ቁጥር የማያስፈልግ ቢሆንም-እንኳን፤ ማመልከቻው - ሂደቱን-ለማከናወን መዘግየት እንዳይኖር ለመከላከል እና የተማሪዎቻችንን፣ የሠራተኞችን እና የማህበረሰቡን ደህንነት-ለማረጋገጥ ትክክለኛ እና የተሟላ መረጃ እንዲኖረን ያስፈልገናል። ፈቃድ-የተሰጠው የበጎ-ፈቃደኝነት ስራ፤ ለሁለት ዓመታት ሕጋዊ-ሆኖ ያገለግላል። ከዚህ-ጊዜ በኋላ ግን፣ እንደገና-ለማደስ እና ለትምህርት ቤቶች እርዳታ-በመስጠት ለመቀጠል፣ እባካችሁ የኦንላይን የበጎ-ፈቃደኝነት ማመልከቻውን ሞልታችሁ-አጠናቅቁ።

የበለጠ-መረጃ ለማግኘት **www.acps.k12.va.us/volunteer**ን ጎብኙ፤ እና የሚከተሉትን አግኙ:

- ለACPS የበጎ-ፈቃድ ሠራተኞች - ጠቃሚ-የሆነ፣ የትምህርት ቤት ቦርድ ፖሊሲዎች
- የACPS የስነ-ምግባር ደንብ/Code of Conduct እና የሚጠበቁባቸው-ነገሮች
- የማመልከቻ ቅጽ እና ተደጋግመው የሚጠየቁ ጥያቄዎች
- በአሁኑ-ጊዜ ስለሚገኙ የበጎ-ፈቃደኝነት ስራ ዕድሎች - የሚናገር መረጃ

**Questions?**

- Write to Volunteer@acps.k12.va.us
- Call 571-547-1697

# የበጎ-ፈቃድ ሠራተኛ (Volunteer) መሆን

## የበጎ-ፈቃድ ሠራተኛ (Volunteer)፣ ማን ነው?

የበጎ ፈቃድ-ሠራተኛ (volunteer)፤ በትምህርት ቤት ክፍል/division ውስጥ ተቀጣሪ-ያልሆነ፣ ነገር-ግን በACPS የበጎ ፈቃድ-ስራ አገልግሎትን - ለመስጠት የተፈቀደለት ማንኛውም-ግለሰብ ነው። የበጎ ፈቃድ-ሠራተኛ (volunteer) ሆኖ የሚያካትተው፤ ከትምህርት ቤት ሠራተኞች ቀጥተኛ-የሆነ ቁጥጥር ላይኖረው-በሚችል ሁኔታ - ማንኛውም ቀጣይነት-ባለው ሁኔታ፣ ከACPS ተማሪዎች ጋር አገልግሎቶችን የሚሰጥ ወይም የእርስ-በርስ ግንኙነቶችን የሚያደርግ ሰው-ነው። ሁሉም የበጎ-ፈቃድ ሠራተኞች (volunteers) - በትምህርት ቤት ውስጥ ከመጀመሪያው የበጎ-ፈቃድ ስራቸው በፊት - ማመልከት እና ፈቃድ-ማግኘት አለባቸው፤ እና በ ACPS የትምህርት ቤት ቦርድ ፖሊሲዎች እና በACPS የበጎ-ፈቃድ ሠራተኛ (Volunteer) የስነምግባር ደንብ/Code of Conduct እና የሚጠበቁባቸው-ነገሮች ተገዢ-መሆን አለባቸው።

የበጎ-ፈቃደኝነት ስራዎች የሚከናወኑት - በACPS ትምህርት ቤቶች እና ተቋሞች ውስጥ፣ እንዲሁም-ደግሞ በመስክ-ጉዞዎች (field trips)፣ ዝግጅቶች እና እንቅስቃሴዎች በሚደረጉባቸው በACPS ሠራተኛ-በተመደቡ ቦታዎች ላይ ይካሄዳል። የበጎ-ፈቃድ እንቅስቃሴዎች - አንዳንድ ምሳሌዎች፣ የሚከተሉትን ያካትታል:

- የመስክ-ጉዞ የክትትል-ማድረግ ስራን የሚሰሩ/**Field Trip Chaperones:** ሎጅስቲኮችን በማቀድ፣ ተማሪዎችን በመቆጣጠር እና እንደ የባንድ ዝግጅቶች/band events በመሣሰሉት ላይ ለአንድ-ቀን በመገኘት መርዳት።
- በቀለም-ትምህርት ወይም የመካሪነት-ስራን በመስራት መርዳት: ከተማሪዎች ጋር - ንባብን-ለእነርሱ በማንበብ መሣተፍ፣ እንደ ንባብ፣ ሂሳብ እና ሣይንስ በመሳሰሉት የትምህርት-ዓይነቶች ላይ ማስጠናት፣ እና የመካሪነት ወይም የስራ-መስክ መመሪያዎችን በመስጠት - መሣተፍ።
- በዝግጅት-ላይ እርዳታ-መስጠት: በ'የሣይንስ ትዕይንት/Science Fair' ላይ - በፕሮጀክት ቁጥጥር አድራጊነት፣ በዳኝነት እና በዝግጅት አቀናባሪነት እገዛ-መስጠት።
- የአትሌቲክ እርዳታ: እውቅና-መስጫዎችን፣ የ'booster club እንቅስቃሴዎችን ወይም በስፖርት ዝግጅቶች ላይ በማስተዋወቅ እገዛ-ማድረግ።
- የአትክልት-ስፍራ ፕሮጀክቶች: በትምህርት ቤት የአትክልት-ስፍራ እንቅስቃሴዎች ውስጥ መሳተፍ፤ መትከል፣ አረም-ማረም እና ልዩ-በሆኑ ፕሮጀክቶችን በሚያካትት-ሁኔታ መሳተፍ።
- አስተዳደራዊ እርዳታ: አስተማሪዎችን - የመማሪያ-ክፍል ቁሳቁሶችን በማሰናዳት እና አጠቃላይ-የሆነ አስተዳደራዊ እርዳታን በመስጠት መርዳት።

## የACPS የበጎ-ፈቃድ ሠራተኛ (Volunteer) እንዴት-መሆን ይቻላል

እንደ የበጎ-ፈቃድ ሠራተኛ (volunteer) ሆኖ በACPS ውስጥ ለማገልገል፣ የሚከተሉትን እነዚህ እርምጃዎች መከተል:

**1. የኦንላይን ማመልከቻ/Online Application:** በ'Raptor Technologies secure platform' አማካኝነት፤ [የኦንላይን (online) የACPS የበጎ-ፈቃድ ስራ ማመልከቻን] ሞልቶ-በማጠናቀቅና እና በማስገባት መጀመር (www.acps.k12.va.us/volunteer)። ይህ የሚያካትተው፤ ከACPS የበጎ-ፈቃድ ሠራተኛ (Volunteer) የስነ-ምግባር ደንብ/Code of Conduct እና የሚጠበቁባቸው-ነገሮች - ጋር መስማማትን-ያካትታል።

**2. የበስተጀርባ ሁኔታዎችን ማረጋገጥ/Background Check**: የወንጀለኛነት እና የወሲብ-ጥቃት ወንጀል - የበስተጀርባ ምርመራ (background check) የሚከናወን ይሆናል። የተመዘገቡ የወሲብ-ጥቃት ወንጀለኞች (registered sex offenders) የሆኑ-አመልካቾች፤ የACPS የተመዘገበ የወሲብ-ጥቃት ወንጀለኞች ማስታወቂያ ፖሊሲ (ACPS Sex Offender Registry Notification Policy (File: KN)ን እና የACPS የተመዘገበ የወሲብ-ጥቃት ወንጀለኞች በትምህርት ቤት ንብረት ፖሊሲ (ACPS Registered Sex Offenders on School Property Policy (File: KNA)ን - መመልከት አለባቸው። አመልካቹ - በ['barrier crime' የተከሰሰ-ከነበረ] - በACPS ፖሊሲዎች ላይ በተዘረዘረው-መሠረት (www.acps.k12.va.us/barrier-crimes) የተከሰሰ ከሆነ፣ ማመልከቻዎቹ ውድቅ-ይሆናል።

**3. ፎተግራፍ ያለው-መታወቂያ/Photo Identification:** ከማመልከቻችሁ አንዱ-ክፍል ሆኖ፤ ፎተግራፍ-ያለበት መታወቂያ (ID)ን - ጫኑ (አፕሎድ-አድርጉ)። [ተቀባይነት ያላቸው ሕጋዊ ሰነዶች] በACPS የበጎ-ፈቃድ ስራ (volunteer) ድህረ-ገጽ ላይ ይገኛል (www.acps.k12.va.us/volunteer)።

**4. የመታወቂያ ማረጋገጫ/ID Verification:** በአንድ ሣምንት ውስጥ፣ አብዛኛዎቹ አመልካቾች - ለመታወቂያ ማረጋገጫ የአምስት-ደቂቃ የርቀት ቀጠሮ/virtual appointment ለመያዝ፤ በተለይም ከACPS 'Raptor Volunteer Management system' - የኢሜል መልዕክት ይደርሳቸዋል። ፎተግራፍ-ያለበት መታወቂያችሁ (ID) እና ካሜራ እና ማይክሮፎን ያለው - እንደ ሞባይል ስልክ፣ ታብሌት ወይም ኮምፒውተር ያለ-ዲቨይስ፣ ያስፈልጋችኋል። በአካል-ቀርቦ የመታወቂያ ማረጋገጫ/ID Verificationን ለማድረግ፣ የበጎ-ፈቃድ ሠራተኛ ቢሮ/Volunteer Officeን በአነጋገር - ቀጠሮው ሊያዝ ይችላል (ዝርዝሮቹ በገጽ 2 ላይ ይገኛል)።

**5.** የማጽደቂያ የጊዜ-አቀማመጥ ይህ ሂደት - በተለመደ-ሁኔታ፣ ማመልከቻው ከገባ በኋላ - ከ7-10 የስራ-ቀናትን ይወስዳል። የማጽደቂያው የጊዜ-አቀማመጥ፣ በACPS በዓላት፣ በሚዘጉ-ቀናት እና በከፍተኛ-የማመልከቻዎች ብዛት ምክንያት ሊለያይ-ይችላል።

## ስለ **ACPS** የበጎ-ፈቃድ ሠራተኛነት ዕድሎች እንዴት-ማወቅ ይቻላል

የበጎ ፈቃድ ሠራተኞች፣ በትምህርት ቤቶቻችን ውስጥ ሊያገለግሉበት የሚችሉበት እና ተማሪዎቻችንን የሚረዱበት - ብዙ መንገዶች አሉ! እያንዳንዱ ትምህርት ቤት፣ ለአንድ-የተወሰነ ትምህርት ቤት ፍላጎት ላላቸው የበጎ-ፈቃድ ሠራተኞች (volunteers) የተለያዩ ዕድሎች አሉት፤ ወይም የACPS የበጎ-ፈቃድ ሠራተኛ ቡድን፣ ትምህርት ቤትን በመለየት ሊረዳ ይችላል።

በጎ-ፈቃድ ስራውን ለመስራት ከተፈቀደ-በኋላ፣ ስለ ልዩ የበጎ ፈቃድ ስራው ስለሚፈለግባቸው ነገሮች እና ስለ ፕሮግራሙ ለማወቅ፣ ቃል--የተገባለት የጊዜ-አቀማመጥ እና ሌሎች ተጨማሪ ዝርዝሮችን ለማግኘት፤ ወደ መረጡት ትምህርት ቤት ቀርበው-እንዲያነጋግሩ ይበረታታሉ። ስለ የበጎ-ፈቃድ ሠራተኛ (volunteer) ያሉንን ፍላጎቶች በተመለከተ የሚሰጡ መረጃዎች፣ በትምህርት ቤቱ በራሪ-ወረቀት/newsletter ውስጥ ሊካተት የሚችል፣ ወይም-ደግሞ በኢሜል መልዕክቶች ለቤተሰቦች ሊላኩ የሚችሉ፣ ወይም በትምህርት ቤት የወላጅ-አስተማሪ ማኅበራት (Parent-Teacher Associations (PTA) ወይም በአሌክሳንድርያ ከተማ ካውንስል ፒቲኤዎች (Alexandria City Council of PTAs (PTAC) አማካኝነት ሊጋሩ-ይችላሉ። አስተማሪዎች፤ ስለ ክፍል-እንቅስቃሴዎች እንደ ለተማሪዎች ንባብ-ማንበብ ወይም የመስክ ጉዞዎች ላይ ክትትል-የማድረግ ስራን - ለቤተሰቦች በኢሜል አማካኝነት ወይም ማንቂያዎች/alertsን በመላክ ሊያሳውቁ ይችላሉ። አንዳንድ የበጎ-ፈቃድ የስራ ዕድሎች (volunteer opportunities) በኢሜል አማካኝነት - ከክፍሉ/division የበጎ-ፈቃድ ሠራተኛ የመረጃ-ስብስብ (volunteer database) ውስጥ ወይም በ[www.acps.k12.va.us/volunteer](http://www.acps.k12.va.us/volunteer) ላይ ፖስት-የሚደረግ እና በ‘Volunteer Alexandria’ (www.volunteeralexandria.org) አማካኝነት-ይጋራል።

አንዳንድ የACPS የማህበረሰብ አጋሮች፣ በትምህርት ቤቶቻችን ውስጥ የተቀረጹትን ፕሮግራሞች ይቆጣጠራሉ። በእነዚህ ፕሮግራሞች ለመሳተፍ ፍላጎት ያላቸው - የበጎ-ፈቃድ ሠራተኞች፣ ያንን ድርጅት በቀጥታ ማነጋገር አለባቸው። ለምሳሌ፣ በሁሉም የACPS የመጀመሪያ-ደረጃ ትምህርት ቤቶች ውስጥ - የ‘Alexandria Tutoring Consortium’s Book Buddies’ ፕሮግራም እና የአሌክሳንድሪያ መካሪነት-አገልግሎት አጋርነት/Alexandria Mentoring Partnership - የተለያዩ የታዳጊ-ወጣቶች የመካሪነት ዕድሎችን ይሰጣል። ከማህበረሰብ አጋሮቻችን ጋር የሚሰሩ - በጎ ፈቃድ ሠራተኞች፣ የACPS የበጎ-ፈቃድ ማመልከቻ እና የማፅደቅ-ሂደትን እንዲያጠናቅቁ አሁንም-ቢሆን እንደሚጠበቅባቸው - እባካችሁ አስታውሱ።

# ለACPS የበጎ-ፈቃድ ሠራተኞች (Volunteers) የሚጠበቁባቸው-ነገሮች

## የACPS የበጎ-ፈቃድ ሠራተኛ (Volunteer) የስነምግባር ደንብ/Code of Conduct እና የሚጠበቁባቸው-ነገሮች

የACPS  በጎ-ፈቃድ ሠራተኞች፣ በማመልከቻው-ሂደት ውስጥ፣ የACPS የበጎ ፈቃድ ሠራተኛ የስነ-ምግባር ደንብ እና የሚጠበቁባቸው-ነገሮች (Code of Conduct & Expectations)ን - ማንባብና መፈረም ያስፈልጋቸዋል። የበጎ-ፈቃድ ሠራተኞች፣ ከሁሉም የACPS ቦርድ ፖሊሲዎች እና መስፈርቶች ጋር - ይህን የስነ-ምግባር ደንብን ጨምሮ - እራሳቸውን-ማስተዋወቅ እና ተገዢ-እንዲሆኑ ይጠበቅባቸዋል። በዚህ የመጠቀሚያ መጽሐፍ/handbook ውስጥ በአጠቃላይ-ይዘቱ ቅጂው-እንዲዘጋጅ የተደረገ እና በኦንላይን/online ላይ - በበርካታ ቋንቋዎች - የሚገኝም-ነው (www.acps.k12.va.us/volunteer)። ሁሉም የACPS ትምህርት ቤት ቦርድ ፖሊሲዎች - በwww.acps.k12.va.us/school-board/school-board-policies ላይ ይገኛሉ።

የACPS የበጎ ፈቃድ ሠራተኞች የስነ-ምግባር ደንብ (Code of Conduct) በበጎ ፈቃደኝነት በሚሰሩበት ጊዜ በበጎ-ፈቃደኝነት ባህሪይ፣ የተማሪ ግላዊነት/student privacy፣ በተማሪ ላይ የሚደርስ ጥቃትን የሚመለከቱ ጉዳዮች ካሉ፤ ከባለስልጣናት ጋር የመነጋገርን-አስፈላጊነት እና ሌሎችንም-ተጨማሪ ነገሮች ይዘረዝራል። የበጎ-ፈቃድ ሠራተኞች፣ ስለዚህ የስነ-ምግባር ደንብ (code of conduct) ወይም ተገቢ-የሆነ ባህሪይ ውስጥ-ስላለው ማንኛውም-ዓይነት ጥያቄዎች ካላቸው፤ የትምህርት ቤቱን አስተዳዳሪ ወይም የACPS  የበጎ-ፈቃድ ሠራተኛ ባለሞያ (Volunteer Specialist)ን ማነጋገር አለባቸው።

የACPS የበጎ-ፈቃድ ሠራተኛ (Volunteer) የስነምግባር ደንብ/Code of Conduct እና የሚጠበቁባቸው-ነገሮችን ላይ ጥሰቶች ሲኖሩ፣ በትምህርት ቤት አመራር - በመጀመሪያ ምላሽ-የሚሰጥበት ይሆናል። አንድ-ነጠላ የሆነ ጥሰት ወይም ፓተርን ያላቸው ጥሰቶች ሲከሰት፣ የበጎ-ፈቃድ ሠራተኛን መብቶች ጊዜያዊ-እገዳ ወይም መቋረጥ ዋስትና-የሚሰጥ የውሳኔ ደረጃን የሚሰጥ ክፍል-አቀፍ (division-wide) የምልከታ-ሂደት በዘርፍ-የሚመለከት አለ።

# የACPS የበጎ-ፈቃድ ሠራተኛ (Volunteer) የስነምግባር ደንብ/Code of Conduct እና የሚጠበቁባቸው-ነገሮች

ይህ ሰነድ፣ ከACPS የቦርድ ፖሊሲ “KK-School Visitors & Volunteers”፣ ጋር ጎን-ለጎን በመሆን፤ በትምህርት ቤቶቻችን ውስጥ - የተማሪዎችን እና የሠራተኞችን ደህንነት-መጠበቁን በማረጋገጥ-ላይ እርዳታ እንዲያደርጉ፤ ከአሌክሳንድሪያ ከተማ የሕዝብ ትምህርት ቤቶች (Alexandria City Public Schools (ACPS) የበጎ-ፈቃድ ሠራተኞች (volunteers) የሚጠበቅባቸውን-ነገሮች ያብራራል። በተጨማሪም፤ የበጎ-ፈቃድ ሠራተኞች (volunteers)ን፣ የ‘ACPS Volunteer Handbook’ን እንዲመለከተቱ እና ተገዢ-እንዲሆኑ፣ ACPS ይጠይቃል።

የACPS የበጎ-ፈቃድ ሠራተኛ (volunteer) እንደ-መሆኔ፤ በሚከተሉት የበጎ-ፈቃድ ሠራተኞች የስነምግባር ደንብ (Volunteer Code of Conduct) እና የሚጠበቁባቸው-ነገሮችን ላይ በሕጉ-ተገዢ ለመሆን ተስማምቻለሁ:

1. በአካል-ተገኝቶ (in-person)ም ወይም በርቀት (virtually)ም ሆነ - እንደ የበጎ-ፈቃድ ሠራተኛ (volunteer) በመሆኔ፤ በትምህርት ቤቱ ከተመደበው ሠራተኛ እና/ወይም በACPS የማህበረሰብ አጋርነቶች እና ተሣትፎ ቢሮ (Office of Community Partnerships and Engagement) ፈቃድ-በተሰጣቸው የACPS አጋሮች - አማካኝነት - ማስተባብርን የማከናውን እና ትዕዛዞችንም የማገኝ መሆን-አለብኝ።

2. ወዲያውኑ የበጎ-ፈቃደኝነት በምሰጥበት የACPS ተቋም እንደደረስኩኝ፣ በዋናው-ቢሮ ወይም ለመፈረም በተዘጋጀው ጣቢያ ላይ መግባቴን ያማሳውቅ እና ፎተግራፍ-ያለበት መታወቂያ (ID)ን ስካን/scan ማድረግ አለብኝ። የበጎ-ፈቃድ ሠራተኛ (volunteer) መሆኔን ማሳወቂያ-የሆነውን ተለጣፊ (sticker)፤ በACPS ውስጥ የበጎ-ፈቃድ ስራን በማከናውንበት ጊዜ-ሁሉ አደርጋለሁ። የበጎ-ፈቃድ ስራዬን እንደአጠናቀኩኝ፣ መውጣቴን በፊርማ-አረጋግጣለሁ።

3. በስራ-ገበታዬ መገኘት (attendance) ላይ፣ በቅልጥፍና እና በተደጋጋሚነት-በመገኘት አሳያለሁ። የማረፍድወይም የምቀር ከሆነ፤ በተቻለ-ፍጥነት - ለትምህርት ቤቱ የበጎ-ፈቃድ አስተባባሪ ወይም የተወከለው ለአገልግሎት-ሰጪ የክፍል-ሠራተኛው ማሳወቅ-አለብኝ።

4. ከትምህርት ቤቱ የበጎ ፈቃደኞች አስተባባሪ፣ ተቆጣጣሪው አስተማሪ ወይም የሰራተኛ አባል እና/ወይም የአጋር ድርጅት - ግንኙነት-ለማድረግ፣ ጥያቄው-እንደቀረበ፤ ወዲያውኑ ምላሽ እሰጣለሁ።

5. አዎንታዊ አመለካከትን ጠብቄ-እሰራለሁ፣ እና ማንኛውንም ስጋቶችን ወይም የአቤቱታ-ቅሬታዎችን፣ በፍጥነት እና በአክብሮት - ለሚመለከተው ሰራተኛ ወይም አስተዳደር አስተላልፋለሁ።

6. በማንኛውም ጊዜ፣ በACPS ባለስልጣናት ወይም በሕግ-አስከባሪዎች ካልተነሳሳ-በስተቀረ፣ የተማሪውን ግላዊነት (privacy) እና ሚስጥራዊነት (confidentiality)ን እጠብቃለሁ።

7. የምሣተፍበትን የበጎ-ፈቃደኝነት እንቅስቃሴን በተመለከተ፣ የተማሪ ደህንነት እና/ወይም ከደህንነት-ጥበቃው ጋር በተያያዘ ማንኛውም-ስጋቶች ካሉኝ፤ ከACPS አስተማሪዎች እና/ወይም የትምህርት ቤት አስተዳደሮች አጋራለሁኝ።

8. አንድ-ልጅ ወደ እኔ መጥቶ ስለደረሰበት የጥቃት ሁኔታ ከተናዘዘ ወይም በልጁ ላይ የጥቃት ምልክቶችን ወይም ጠቋሚ-የሆኑ ነገሮችን ካየሁኝ፤ የትምህርት ቤቱን አስተዳደር አሳውቃለሁ። ተገቢ-ለሆኑ ባለስልጣናት - እንደየ-አስፈላጊነቱ፣ መረጃዎችን ለማጋራት እራሴን ዝግጁ-አደርጋለሁ፤ ይህም ከACPS ሠራተኞች ጋር አብሮ-በመተባበር ባለስልጣኖችን እንዲገኙ ማድረግን ይጠበቅብኝ-በሚችል ሁኔታ ላይ ነው። የ[‘Commonwealth of Virginia’ አትሌቲክ በጎ-ፈቃድ ሠራተኞች (athletic volunteers)፣ በግዳጅ የሚሰሩ ዘጋቢዎች አድርጎ እንደሚቆጥራቸው]፣ እገነዘባለሁ።

9. በምድብ ትምህርት ቤት ወይም መምሪያው ውስጥ፤ ሁሉንም የACPS ደንቦች እና ክንውኖችን አከብሬ-እከተላለሁ።

10. በትምህርት ቤቶች ውስጥ የበጎ-ፈቃደኝነት ስራን በምሰራበት-ጊዜ፣ የአዋቂዎች የመጸዳጃ-ቤትን ብቻ እጠቀማለሁ።

11. ከማንኛውም ግለሰብ ተማሪ ጋር ለብቻ-መሆንን አስወግዳለሁ።

12. በACPS ውስጥ የበጎ-ፈቃደኝነት ስራ እየሰራሁ ባለሁበት ጊዜ፣ ማንኛውንም ተማሪ ዲስፕሊን/discipline አላደርግም። ለምሳሌ-ያህል - አስቸጋሪ-የሆነ ባህሪይ ያለውን ተማሪ፤ ከአስተማሪ ወይም የትምህርት ቤት ሠራተኛ ወዲያውኑ እርዳታ-ለማግኘት እጠይቃለሁ።

13. ከተማሪው ወላጆች/አሳዳጊዎች ፈቃድ ካላገኘሁ በስተቀረ፤ ተማሪዎችን ከትምህርት ቤት ሰዓታት ውጪ አላነጋግርም።

14. ለተማሪዎች፣ የገንዘብ-ሽልማቶች (monetary rewards) ወይም ስጦታዎችን አልሰጥም። አንዳንድ-ተማሪዎች የምግብ አለርጂዎች ወይም የአመጋገብ እገዳዎች ሊኖሯቸው ስለሚችል፤ ምግብን ለተማሪዎች አላቀርብም/አላጋራም።

15. ACPS - ተማሪዎቻቸውን፣ የማስወጣት (opt-out የማድረግ) ዝርዝር ውስጥ ስለማስገባት የእያንዳንዱ ቤተሰብ ውሳኔ የሚያከብር በመሆኑ፤፣ እኔ እንደ በጎ ፈቃድ-ሠራተኛነቴ በምሳተፍበት ጊዜ፣ የተማሪዎችን ምስሎች በማህበራዊ-ሚዲያ ላይ መለጠፍን ጨምሮ ስለተማሪዎች ወይም ስለ ሌሎች - የተማሪ ፎቶግራፎችን ወይም የግል-መረጃዎችን አልገልጽም፣ አልጠቀምም ወይም አላሰራጭም። የአጋር ድርጅት ሠራተኞች (Partner organization staff)፣ የACPS ተማሪዎችን ለሚያካትቱ ፎቶዎች/ቪዲዮዎች ቅድመ-ፍቃድ ማግኘት አለባቸው።

16. ማንኛውንም የርቀት ክፍለጊዜዎች/virtual sessionsን አልቀዳም (record አላደርግም)። ይህን ማድረግ፣ ወዲያውኑ ከበጎ-ፈቃድ ሠራተኝነት መባረርን ያስከትላል።

17. የበጎ ፈቃደኝነት-ስራን በምሠራበት-ጊዜ፣ በአደገኛ ዕፅ ወይም በአልኮል-መጠጥ ተጽዕኖ-ስር አልሆንም ወይም የበጎ-ፈቃደኝነት ስራን በምሠራበት-ጊዜ አደንዛዥ ዕፅ ወይም አልኮል-መጠጥን አልጠቀምም።

18. በቨርጅኒያ ኮድ (Code of  Virginia) ስር - ማገጃን የሚያካትት - ማንኛውንም የጥፋት ወንጀል ውስጥ የተወነጀልኩኝ ከሆነ፣ ለትምህርት ቤቱ ርዕሰ-መምህር ወይም ተገቢ-ለሆነ የመምሪያ ዋና-ኃላፊ - ወዲያውኑ አሳውቃለሁ።

19. ሁሉንም ተማሪዎች፤ ከACPS ቃል-ገብሎት ከሚሰራበት ከACPS 2025 ስልታዊ-ዕቅድ (Strategic Plan) ፍትሃዊ-እኩልነት እና ስብጥርነትን-ማክበር ጋር ጎን-ለጎን በሚሄድ ሁኔታ - አከብራለሁ።

20. የ'ACPS' ሠራተኛ - ትዕዛዞችን እና መመሪያዎችን ተከትዬ-አከብራለሁ።

21. የ'ACPS የወሲባዊ ጥቃት ፖሊሲ/Sexual Harassment policy (GBAA/JFHA)ን፣ አነባለሁ እና ሕጉን-እከተላለሁ።

22. የ'ACPS የጦር-መሣሪያዎችን በትምህርት ቤት ውስጥ ፖሊሲ/Weapons in School policy (JFCD)ን፣ አነባለሁ እና ሕጉን-እከተላለሁ።

23. በበጎ-ፈቃደኝነት የስራ-ተሞክሮዬ ወቅት የACPS ኮምፒውተሮችን ወይም ሶፍትዌር (software)ን የምጠቀም-ከሆነ፤ የ'ACPS ኃላፊነት-አለው የኮምፒውተር ዘዴ አጠቃቀም ፖሊሲ/Responsible Computer System Use policy (IIBEA/GAB)'ን፣ አነባለሁ እና በህጉም-እገዛለሁ።

ለACPS እገዛ-ለማድረግ፤ ጊዜዬን፣ ጥረቴን እና አገልግሎቴን ነፃ-ሆኜ እንደምሰጥ እውቅና-እሰጣለሁ እና ለዚህም-ምንም የአገልግሎት ክፍያ እንደማልቀበል - ተረድቻለሁ። እንደ የበጎ-ፈቃድ ሠራተኛ በማገለግል ጊዜ፤ ምንም-ዓይነት ሊደርስብኝ በሚችል - ጉዳት፣ አደጋ ወይም ሌሎች ያልተጠበቁ-ሁኔታዎች ምክንያት ያጋጠመኝን የሕክምና-ክፍያዎችን ለማግኘት - በማንኛውም ለሠራተኛ-የሚሰጥ ካሳ ወይም ተመሳሳይ የሆነ ኢንሹራንስ-ሽፋን ስር እንዳልሆንኩኝ አውቄአለሁ።

ምንም-እንኳን ለጉዳት የመጋለጥ አደጋ እንዳለ እና ከ'ACPS' ለሠራተኞች-የሚሰጥ ካሳ ወይም ሌላ የህክምና ኢንሹራንስ ሽፋን ባይኖረኝም-እንኳ፤ በ'ACPS' ላይ ማንኛውንም እና ሁሉንም የይገባኛል-ጥያቄዎችን፣ እርምጃዎች፣ ወይም የእርምጃ መውሰድ መንስዔዎችን - አውቄ እና ፈቃደኛ-በመሆን የማልጠይቅ-መሆኔን፤ ለACPS የበጎ-ፈቃደኝነት የስራ-እንቅስቃሴን በማደርግበት ጊዜ - ሊደርስብኝ ለሚችለው ጉዳት ወይም አደጋ፤ ACPSን፣ ባለድርሻዎቹን፣ ወኪሎቹን፣ ተባባሪዎቹን እና ተቀጣሪ-ሠራተኞቹን፣ ኃላፊ-እንዲሆኑ አላደርግም።

በሁሉም ጊዜያቶች፣ የ**ACPS** የበጎ-ፈቃድ ሠራተኛ **(Volunteer)** የስነምግባር ደንብን እና የሚጠበቁ-ነገሮችን - ለመከተል ተስማምቻለሁ። የ**ACPS** የበጎ-ፈቃድ ሠራተኛ  የስነምግባር ደንብ **(Volunteer Code of Conduct)**ን እና የሚጠበቁ-ነገሮችን - አለመከተል፤ የበጎ-ፈቃድ ሰዓቴ ላይ ግደባዎችን ሊያስከትል የሚችል ወይም-ደግሞ ከበጎ-ፈቃድ የስራ-ድርሻዬ መባረርን ሊያስከትል እንደሚችል ተረድቻለሁ።

- ስም *
- ኢሜል *

## በትምህርት ቤቶች ውስጥ - መግባት/መውጣት (Checking In/Out)

የበጎ ፈቃደኝነት አገልግሎት ለመስጠት - የበጎ-ፈቃድ ሠራተኛው ወደ ትምህርት ቤት ሪፖርት ባደረጉ-ቁጥር፤ በትምህርት ቤቱ በዋናው ቢሮ ውስጥ-ገብተው ስማቸውን አስገብተው - ፎተግራፍ-ያለበት መታወቂያቸውን (ID)ን ለጎብኚዎች እና ለበጎ-ፈቃድ ሠራተኞች በተመደበው ኪዮስክ (kiosk)ን በመጠቀም ስካን/scan አድርገው መገኘታቸውን-ማሳወቅ አለባቸው። መግባታቸውን በሚያረጋግጡበት ጊዜ-ላይ፣ የበጎ-ፈቃድ ሠራተኛ የሚለጠፍ-ባጅ/sticker badge - በትምህርት ቤቱ ውስጥ ለምን ያህል ጊዜ እንደሚቆዩ በግልጽ-የሚያሳየውን - ሲስተሙ/system ያትማል። ለደህንነት እና ለጥበቃ ዓላማ-ሲባል፤ የበጎ-ፈቃደኝነት አገልግሎት ጊዜያቸውን ጨርሰው በሚወጡበት ጊዜ፣ በዚህ ኪዮስክ (kiosk) ውስጥ መውጣታቸውን እባካችሁ እንድታረጋግጡ እንጠይቃችኋለን።

## ስጋቶችን-ሪፖርት ማድረግ

የበጎ-ፈቃድ ሠራተኞች - ስለ ተማሪ፣ የሠራተኛ አባል ወይም ስለ-እንቅስቃሴው ስጋቶች ካላቸው፤ እነዚህን ስጋቶች - የበጎ-ፈቃድ ሠራተኛው ወደ የትምህርት ቤቱ የበጎ-ፈቃድ ሠራተኞች ግንኙነት-ክፍል፣ ርዕሰ-መምህር ወይም ወደ ሌላ የትምህርት ቤት የአመራር-አባል - በአስቸኳይ ምላሽ-እንዲሰጥበት፣ መጠየቅ አለበት። በACPS የበጎ-ፈቃደኝነት የስነ-ምግባር ደንብ/Code of Conduct እና

የሚጠበቁባቸው-ነገሮች ላይ እንደተገለጸው፤ አንድ ልጅ አለአግባብ-ስለሆነ የጥቃት ሁኔታ ሲናገር ወይም በልጁ ላይ የጥቃት-ምልክቶችን ወይም ጠቋሚ-ነገሮች የበጎ-ፈቃድ ሠራተኛው ከተመለከተ - ወደ የትምህርት ቤት አስተዳዳሪው ማሳወቅ ይጠበቅባቸዋል። አስፈላጊ-ከሆነ፤ ሁሉ የበጎ-ፈቃድ ሠራተኞች - መረጃዎችን ተገቢ-ከሆኑ ባለስልጣናት ጋር ለማጋራት እራሳቸውን የሚገኙ-ማድረግ ይጠበቅባቸዋል። በ‘Commonwealth of Virginia’ አትሌቲክ በጎ-ፈቃድ ሠራተኞች (athletic volunteers)፣ በግዳጅ የሚሰሩ ዘጋቢዎች ተደርገው ይቆጠራሉ።

# ለACPS የበጎ-ፈቃድ ሠራተኞች - ፖሊሲዎች እና የክንውን-ሂደቶች

የሚከተሉት ፖሊሲዎች፣ እዚህ ተጠቃለው-ቀርበዋል፤ ሁሉም ሙሉ-በሙሉ በACPS የትምህርት ቤት ቦርድ ፖሊሲ ድህረ-ገጽ (www.acps.k12.va.us/school-board/school-board-policies) ላይ ይገኛል።

## ትምህርት ቤት ጎብኚ-እንግዶች እና የበጎ-ፈቃድ ሠራተኞች፣ (ፖሊሲ/Policy KK)

የበጎ-ፈቃድ ሠራተኞች (Volunteers)፤ በአካል-በመገኘትም (in-person) ወይም በርቀት (virtually)ም ሆነ - በACPS አማካኝነት የቅንብር-አሰራር እና ትዕዛዞችን የሚያገኙ እና በማህበረሰብ አጋርነቶች እና ተሣትፎ ቢሮ (Office of Community Partnerships and Engagement) ፈቃድ-ማግኘት አለበት። ከበጎ-ፈቃድ ስራዎች ጋር ተያያዥ-የሆኑ ፕሮቶኮሎች እና ሂደቶች፤ አስፈላጊ-የሆኑ የቀደመ ሁኔታን ማረጋገጫዎች (background checks) እና ምርመራ-ማድረጊያዎችን ጨምሮ - በACPS የበጎ-ፈቃድ ሠራተኛ (Volunteer) የስነ-ምግባር ደንብ/Code of Conduct እና የሚጠበቁባቸው-ነገሮች የሚተዳደር ሲሆን፣ ይህም ሚስጢራዊነትን የመጠበቅ ድንጋጌ ጋር መገዛትን የሚያካትት-ነው።

## የወሲብ ትንኮሳ/Sexual harassment (Policy GBAA/JFHA)

ACPS፤ በዘር፣ በብሔር፣ በጉዳተኝነት፣ በሃይማኖት፣ በፆታ፣ በፆታ-ማንነት፣ በፆታ-አገላለጽ ወይም በፆታዊ-ዝንባሌ ላይ የተመሰረተ - ትንኮሳ እና ወሲባዊ-ትንኮሳ የፀዳ፣ የትምህርት/የስራ አካባቢን ለመጠበቅ በቁርጠኝነት-የሚሰራ ነው። ስለሆነም፤ የአሌክሳንድሪያ ከተማ ትምህርት ቤት ቦርድ - በዘር፣ በብሔር፣ በጉዳተኝነት፣ በሃይማኖት፣ በጾታ፣ በፆታ-ማንነት፣ በፆታ-አገላለጽ ወይም ጾታዊ ትንኮሳን - በማንኛውም ተማሪ ላይ ወይም በትምህርት ቤት ሠራተኞች ላይ፣ ወይም በማንኛውም በትምህርት ቤት ስፖንሰር በተደረጉ እንቅስቃሴዎች ላይ እንዳይከሰት ይከለክላል።

## የጦር-መሣሪያዎች (Weapons)፣ በትምህርት ቤቶች ውስጥ (Policy JFCD)

ማንኛውም ሰው፣ ተማሪዎችን ወይም ሠራተኞችን ጨምሮ - በዚህ ፖሊሲ ውስጥ እንደተገለጸው፤ በትምህርት ቤት ንብረት ውስጥ - በህግ ከተፈቀዱ ውሱን-ሁኔታዎች በACPS ድህረ-ገጽ ልዩ-በሆነ ሕጋዊ-ፍቀድ አግኝተው ፖስት ከተደረገው ዝርዝር ካልሆነ-በስተቀረ፤ ማንኛውምን የጦር-መሳሪያን - ማምጣት፣ መጠቀም ወይም መያዝ አይፈቀድም።

## ኃላፊነት-ያለው የኮምፒውተር አጠቃቀም (Policy IIBEA/GAB)

ACPS እና ሠራተኞቹ፤ ቴክኖሎጂን በወጥነት፣ በኃላፊነት እና ውጤታማ-በሆነ መልኩ ለማስተማር እና ለመማር፣ ለመገናኛ እና ለምርታማነት ለመጠቀም - በቁርጠኝነት-ይሰራሉ። የኮምፒዩተር ስርዓቱን-ለማግኘት፤ በመጠቀሚያ የጊዜ-መጠኑ፣ የአጠቃቀም ዓይነት ወይም ይዘት - ላይ፣ አላግባብ-አጠቃቀም - መጠቀም የለበትም። የACPS የኮምፒዩተር ስርዓትን የሚጠቀሙ ማንኛውም ግለሰብ፣ ስለዚያ አጠቃቀም በተመለከተ ስለአለው ግላዊነት/privacy መጠበቅ-ኃላፊነት የለውም።

## ማህበራዊ ሚድያ (Social Media)ን መጠቀም

የACPS ፖሊሲ - ኃላፊነት-ያለው እና ደህንነቱ-የተጠበቀ የማህበራዊ ሚዲያ አጠቃቀም እና ተዛማጅ ቴክኖሎጂዎችን፤ በተማሪዎች፣ ሠራተኞች እና የበጎ-ፈቃድ ሠራተኞች ላይ ምላሽ-ይሰጣል። የበጎ-ፈቃድ ሠራተኞች፤ ሚስጥራዊነትን፣ የተማሪን ግላዊነት/student privacy እና የቤተሰብ ፍቃድ-መስጫዎችን - በሚዲያ መውጫ (opt-outs) ላይ እንደተገለጸው-ሁሉ፣ የተማሪዎችን ፎቶዎች በማህበራዊ-ሚዲያ ላይ - የበጎ-ፈቃድ ሠራተኞች ፖስት-ለማድረግ - ACPS አይፈቅድላቸውም። የማህበረሰብ አጋሮች፤ ለማንኛውም ለሚያስፈልጋቸው - ፎተግራፍ፣ ቪዲዮ እና ማህበራዊ ሚዲያ - ከግንኙነት-ክፍል ቢሮ (Office of Communications) ጋር መስራት አለባቸው። ተጨማሪ-መረጃን ለማግኘት፣ እባካችሁ በwww.acps.k12.va.us/policies-GAC ተመልከቱ።

# ከተማሪዎች እና ቤተሰቦች ጋር የበጎ-ፈቃድ ሠራተኛው ግንኙነቶች

የበጎ-ፈቃድ ሠራተኞች፣ በACPS ውስጥ - በበጎ-ፈቃድ ሠራተኞች፣ በሠራተኞች፣ በተማሪዎች እና በቤተሰቦች መካከል - አዎንታዊ ግንኙነት ለመፍጠር ቁልፍ የሆኑትን ጉዳዮች በሚመለከት ምላሽ-በሚሰጠው፤ በACPS - የበጎ-ፈቃድ ሠራተኛ (Volunteer) የስነምግባር ደንብ/Code of Conduct እና የሚጠበቁባቸው-ነገሮች - መገዛት-አለባቸው። ከሌሎች ጉዳዮች ጎን-ለጎን ሆኖ፤ ይህም የበጎ-ፈቃድ ሠራተኞች የተማሪን ግላዊነት እና ሚስጢራዊነትን ማክበርን ጨምሮ፣ ከተማሪው ጋር ለብቻ-መሆንን ማስወገድ ወይም ማንኛውንም የዲስፕሊን እርምጃን

አለመውሰድ፣ አዎንታዊ አመለካከትን ጠብቆ-መቆየትን፣ ስለ ማንኛውም ስጋቶች ወይም ችግሮች ከትምህርት ቤት ሠራተኛ ጋር መነጋገርን፣ እና ከቤተሰብ ፈቃድ-ሳያገኙ ከትምህርት ቤት ሰዓታት ውጪ ተማሪዎችን አለማነጋገርን - ያካትታል።

## ከተማሪዎች እና ቤተሰቦች ጋር የበጎ-ፈቃድ ሠራተኛው ግንኙነቶች

የበጎ-ፈቃድ ሠራተኞች፣ በACPS ውስጥ - በበጎ-ፈቃድ ሠራተኞች፣ በሠራተኞች፣ በተማሪዎች እና በቤተሰቦች መካከል - አዎንታዊ ግንኙነት ለመፍጠር ቁልፍ የሆኑትን ጉዳዮች በሚመለከት ምላሽ-በሚሰጠው፤ በACPS - የበጎ-ፈቃድ ሠራተኛ (Volunteer) የስነምግባር ደንብ/Code of Conduct እና የሚጠበቁባቸው-ነገሮች - መገዛት-አለባቸው። ከሌሎች ጉዳዮች ጎን-ለጎን ሆኖ፤ ይህም የበጎ-ፈቃድ ሠራተኞች የተማሪን ግላዊነት እና ሚስጢራዊነትን ማክበርን ጨምሮ፣ ከተማሪው ጋር ለብቻ-መሆንን ማስወገድ ወይም ማንኛውንም የዲስፕሊን እርምጃን አለመውሰድ፣ አዎንታዊ አመለካከትን ጠብቆ-መቆየትን፣ ስለ ማንኛውም ስጋቶች ወይም ችግሮች ከትምህርት ቤት ሠራተኛ ጋር መነጋገርን፣ እና ከቤተሰብ ፈቃድ-ሳያገኙ ከትምህርት ቤት ሰዓታት ውጪ ተማሪዎችን አለማነጋገርን - ያካትታል።

## ከተማሪዎች እና ቤተሰቦች ጋር የበጎ-ፈቃድ ሠራተኛው ግንኙነቶች

የበጎ-ፈቃድ ሠራተኞች፣ በACPS ውስጥ - በበጎ-ፈቃድ ሠራተኞች፣ በሠራተኞች፣ በተማሪዎች እና በቤተሰቦች መካከል - አዎንታዊ ግንኙነት ለመፍጠር ቁልፍ የሆኑትን ጉዳዮች በሚመለከት ምላሽ-በሚሰጠው፤ በACPS - የበጎ-ፈቃድ ሠራተኛ (Volunteer) የስነምግባር ደንብ/Code of Conduct እና የሚጠበቁባቸው-ነገሮች - መገዛት-አለባቸው። ከሌሎች ጉዳዮች ጎን-ለጎን ሆኖ፤ ይህም የበጎ-ፈቃድ ሠራተኞች የተማሪን ግላዊነት እና ሚስጢራዊነትን ማክበርን ጨምሮ፣ ከተማሪው ጋር ለብቻ-መሆንን ማስወገድ ወይም ማንኛውንም የዲስፕሊን እርምጃን አለመውሰድ፣ አዎንታዊ አመለካከትን ጠብቆ-መቆየትን፣ ስለ ማንኛውም ስጋቶች ወይም ችግሮች ከትምህርት ቤት ሠራተኛ ጋር መነጋገርን፣ እና ከቤተሰብ ፈቃድ-ሳያገኙ ከትምህርት ቤት ሰዓታት ውጪ ተማሪዎችን አለማነጋገርን - ያካትታል።

## የአለባበስ ኮድ **(Dress Code)**

የበጎ-ፈቃድ ሠራተኞች፣ ተቀባይነት-ካለው ማህበራዊ እና የስራ-ቦታ መደበኛ-አለባበሶች ጋር አብሮ በሚሄድ ሁኔታ እንዲለብሱ ይጠበቅባቸዋል። ስለ ተወሰነ ዓይነት አለባበስ እርግጠኛ-ካልሆናችሁ፤ እባካችሁ የACPS የበጎ-ፈቃድ ሠራተኛ ባለሞያ (Volunteer Specialist)ን ወይም የትምህርት ቤት የበጎ-ፈቃድ አስተባባሪን - አነጋግሩ።

## እህትና ወንድሞች/**Siblings**

ታዳጊ-ልጆች - የበጎ-ፈቃድ ስራን በሚሰሩበት-ጊዜ፣ ከቤተሰብ ጋር አብረው መሄድ የለባቸውም። የቅድመ-ትምህርት ቤት ተማሪዎች (Preschool students)/ትናንሽ እህትና-ወንድሞች - ለተማሪዎች፣ ሠራተኞች እና የቤተሰብ የበጎ-ፈቃድ ሠራተኞች - ትኩረትን-የሚበታትኑ ሊሆኑ ይችላሉ። ለእነርሱ-ለራሳቸው ደህንነት-ሲባል በቅርብ-ክትትል የሚያስፈልጋቸው ናቸው፤ እና የቤተሰብ-አባላት እንደ ACPS የበጎ-ፈቃድ ሠራተኞች ሆነው ሲያገለግሉ - ይህንንም-ጨምሮ ማድረግ ከባድ ነው።

## የቢሮ ማሽኖች/Office Machines

የመማሪያ-ክፍል ቁሳቁሶች/classroom materialsን - በማሰናዳት አስተማሪዎችን የሚረዱትን - የበጎ-ፈቃድ ሠራተኞችን፣ ሠራተኞች ያደንቋቸዋል። ሁሉንም የቢሮ መጠቀሚያ ቁሳቁሶችን በትክክለኛው-መንገድ ለመጠቀም፣ የበጎ-ፈቃድ ሠራተኞች ስልጠና-ሊሰጣቸው ይገባል። የበጎ-ፈቃድ ሠራተኞች - ወደ-ጎን ለመሆን-ፈቃደኛ ሆነው፤ አስተማሪዎች ወይም የቢሮ ሠራተኞች - በዕረፍት-ጊዜ ወይም ወዲያውኑ-ማግኘት በሚያስፈልጋቸው-ጊዜ፤ ማሽኖችን እንዲጠቀሙ መፍቀዳቸው በጣም-ጠቃሚ ነው። የACPS መሳሪያዎች/equipment፤ ለትምህርት/ለትምህርት ቤት ዓላማዎች ብቻ የሚውሉ እንጂ፣ ለግል-ጥቅም የሚያገለግሉ አይደሉም።

## የትምህርት ቤት የመኪና-ማቆሚያ ስፍራ

በትምህርት ቤቶች አቅራቢያ ወይም በትምህርት ቤት የመኪና-ማቆሚያ ስፍራ ውስጥ በሚነዱበት-ጊዜ፤ ከፍተኛ-ጥንቃቄ መወሰድ አለበት። አሽከካሪዎች፤ በሁሉም-ጊዜያት - ተማሪዎችን እና ሌሎችን በቅርበት-እየተከታተሉ እንዲያሽከረክሩ እንጠይቃለን። በትምህርት ቤት ውስጥ የበጎ-ፈቃድ ስራን ለመስራት በምትመጡበት-ጊዜ፣ የት-ማቆም እንዳለባችሁ ለማወቅ - ከትምህርት ቤቱ ቢሮ ጋር መረጃዎችን እባካችሁ ጠይቁ።

## ስርቆት

ከትምህርት ቤቱ የበጎ-ፈቃድ ሠራተኞች መሪ ወይም አስተዳዳሪ - ግልጽ-የሆነ ፈቃድ-ሳይኖር፣ በACPS የተገዛ ወይም የሚያቀርብ ማንኛውም-ዕቃ፣ ከትምህርት ቤት መውጣት የለበትም። የበጎ-ፈቃድ ሠራተኞች፣ የበጎ-ፈቃድ አገልግሎት በሚሰጡበት-ጊዜ፣ በግቢያው-ውስጥ - ከመጠን-በላይ የሆነ ገንዘብ ወይም ውድ ዕቃዎችን ይዘው መምጣት የለባቸውም።

## ከስራ-መልቀቅ/መወገድ

ከACPS ጋር፣ በበጎ-ፈቃድ ሠራተኛነት ላለመቀጠል ከወሰናችሁ፤ እባካችሁ በትምህርት ቤቱ ውስጥ አብረው ሲሰሩ ለነበሩት - የግንኙነት-ክፍል ሠራተኛን እና በቀጥታ-አብረው ለሚሰሩዋቸው ሌሎች ሠራተኞች - አሳውቋቸው። ACPS፣ ከማንኛውም ግለሰብ ጋር ያለውን የበጎ-ፈቃደኝነት የስራ-ግንኙነትን፣ የማቋረጥ መብቱ የተጠበቀ መሆኑን - እባካችሁ አስታውሱ። የበጎ-ፈቃድ ሠራተኛውን አገልግሎትን ማገጃ - በጽሁፍ የሚቀርብ ይሆናል።

# ለትምህርት ቤት የበጎ-ፈቃድ ሠራተኞች (Volunteers) - መመሪያዎች/Guidelines

## አጠቃላይ ጥቆማዎች/General Tips

**1.** ትዕግስተኛ መሆን: ከተማሪዎች ጋር ስራን-በመስራት ጊዜ፤ ተመራጭ-የሆነውን አቀራረባችሁን ለማግኘት ጊዜ-ስጡት። ስኬታማ-የሆነ ግንኙነቶችን ለመገንባት፣ ትዕግስት ቁልፍ-ነገር ነው።

**2.** ስሞች/**Names**ን ማወቅ ያስፈልጋል: የተማሪዎችን ስም በትክክል መጥራት እና ስፔል/spell ማድረግ ማወቅ፣ እነርሱ-በሚመጡት መንገድ። የእናንተንም-ስም ማወቃቸውን እና በትክክል-መጥራታቸውንም አረጋግጡ።

**3.** ክብር እና ትህትና: ሁሉንም-ሰው በክብር እና በትህትና ማስተናገድ፣ እና ለእናተም በእንደዚሁ-ዓይነት ሁኔታ መጠበቅ።

**4.** ፍላጎትን ማሳየት: በትኩረት-በማዳመጥ እና በቃላቶቻችሁ እና በድርጊቶቻችሁ አማካኝነት እናንተ-ግድ እንደሚላችሁ በማሳየት - ለተማሪዎች ያላችሁን-ፍላጎት ያሳዩ።

**5.** ስኬትን ማበረታታት: የተማሪውን ስኬቶች፤ ደግፉ እና አክብሩ። ከልብ-በመነጨ እና በተደጋጋሚ ማመስገኛ-ቃላት፣ በራስ-መተማመናቸውን ገንቡ። ጥረት-ማድረግ እና ትኩረትን-መስጠት - ልክ እንደ የክንውን-ሂደትን እንደማሳየት ጥቅም-ያለው መሆኑን - አስታውሱ። በአዎንታዊ-ነገሮች ላይ ትኩረት አድርጉ፣ በአንፃሩ-ደግሞ አሉታዊ-የሆኑትን አሳንሶ-ማየት።

**6.** አንዱን-ከአንዱ ማነፃፀርን ማስወገድ: በተማሪዎች፣ በአስተማሪዎች ወይም ትምህርት ቤቶች መካከል ንጽጽርን-ከማድረግ መቆጠብ።

**7.** ፍትሃዊ-መሆን እና ወጥነት-ያለው መሆን/**Be Fair and Consistent:** ድጋፍ-ሰጪ አካባቢን ለመፍጠት፣ ወጥነት-ያለው አሰራር እና ፍትሃዊነት - በጣም አስፈላጊ ነው።

**8.** ስህተቶችን መቀበል/**Embrace Mistakes:** ስህተቶችን-መስራት፣ የመማር አንዱ-ተፈጥሮአዊ ክፍል-መሆኑን - እውቅና-መስጠት። ተማሪዎች፤ ስህተቶችን እንደ እድሎች-ማግኛ መንገድ አድርገው እንዲመለከቱ አበረታቷቸው፣ እና እናንተ-እራሳችሁ ስህተት-መስራታችሁን አትፍሩት።

**9.** እምነትን መገንባት: በአቀራረባችሁ እና በመለካከታችሁ - ታአማኒነት-ያላችሁ እና እውነተኞች-ሁኑ። እውነተኛ-ከሆናችሁ፤ ተማሪዎች ያምኗችኋል እና ያከብሯችኋል።

**10.** መቅረት-በሚኖር ጊዜ ማሳወቅ/**Communicate Absences:** መቅረት-ካለባችሁ፣ ትምህርት ቤቱን አሳውቁ። ተማሪዎች ባለመገኘታችሁ የሚያዝኑ-ቢሆንም እንኳን፣ በመደወላችሁ ምን-ያህል ግድ እንዳላችሁ በማወቃቸው ያመሰግናሉ።

## የበጎ-ፈቃደኝነት ስራ መረጃ/የሂደት-ክንውን ምልከት-ማድረጊያ ዝርዝር

የበጎ-ፈቃድ የስራ እንቅስቃሴን ከሚቆጣጠሩት - አስተማሪ/የሠራተኛ-አጋል ጋር፣ የሚከተሉትን ማረጋገጥ አስፈላጊ ነው:

- ለበጎ-ፈቃደኝነት ስራ - የሚገኙት የጊዜ-ሰሌዳ የተያዘላቸውን ቀናቶች እና ሰዓታትን።
- በበጎ-ፈቃድ ሠራተኛ እና በተመደበው ሠራተኛ መካከል - ቀጣይነት-ያለው በንግግር-የመግባቢያ ሂደቶችን - (ማለትም፤ መደበኛ ኮንፈረንሶች፣ የስልክ ጥሪዎች፣ ኢሜይሎች፣ ማስታወሻዎች፣ መደበኛ-ያልሆኑ ስብሰባዎች)።
- አስተማሪ/ቁጥጥር-አድራጊ አለቃው በሚቀሩ-ጊዜ፣ አማራጭ ዕቅዶችን ማድረግ።

- የትምህርት ቤት/የመምሪያ ሂደቶች እና ደንቦች (ማለትም፤ የግል ዕቃዎችን ማስቀመጥ፣ የአስቸኳይ የአደጋ-ጊዜ ሂደቶችን... ወዘተ...)
- ስለ የበጎ-ፈቃድ ሠራተኛው አርፍዶ-መድረስ ወይም መቅረት፣ ለትምህርት ቤት/መምሪያ ማሳወቂያ ፕሮቶኮል።

## ከተለያዩ የቀደመ-መነሻዎች (Varied Backgrounds) ከመጡ ተማሪዎች ጋር፣ የእርስ-በርስ ግንኙነት ማድረግ

ACPS - ከ16,000 ተማሪዎች በላይ - ከ119 ሃገራት የመጡትን እና 121 ቋንቋዎችን የሚናገሩትን እያገለገለ-ነው። ባህላዊ ልዩነቶች፣ በተማሪዎች የቀደመ-መነሻ እውቀት፣ የመማር ስልት፣ የባህሪይ አቀራረብ እና የማህበራዊ ችሎታዎች ላይ ጉልህ የሆነ ተጽዕኖ ይኖረዋል። የበጎ-ፈቃድ ሠራተኞች - ከተማሪዎች ጋር ተሳትፎ ሲያደርጉ፣ ባህላዊ የቀደመ-መነሻቸውንን ለመረዳት እና ለማድነቅ ጥረት ማድረግ እና የትምህርት ቤቱን አካባቢ ሲጎበኙ ድጋፍ መስጠታቸው - ጠቃሚ ነው።

# ለበጎ-ፈቃድ ሠራተኞች፣ የACPS ሠራተኞች-የማግኛ አድራሻ

በእያንዳንዱ ትምህርት ቤት ለበጎ-ፈቃድ ሠራተኛ እንቅስቃሴ ወይም ፕሮግራም የተመደበው የሠራተኛ-አባል፣ እንደ ዋናው የግንኙነት-ክፍል ሆኖ የሚያገለግል እና የበጎ-ፈቃድ ሠራተኞችን - በሚኖሯቸው ማንኛውም ጥያቄዎች፣ ስጋቶች እና ችግልቶ ለመርዳት የሚገኝ-ነው። የበጎ-ፈቃድ ሠራተኛ ያቀረበው ስጋት ወይም ጥያቄ - በተመደበው የሠራተኛ-አባል ምላሽ-ሳይሰጠው የቀጠለ-ከሆነ፤ ይህ ችግር ወደ ትምህርት ቤቱ ርዕሰ-መምህር ወይም የትምህርት ቤት አስተዳደር አባል-መቅረብ አለበት። በትምህርት ቤቱ ውስጥ ምላሽ-ያላገኙ ነገሮች፣ ወደ የACPS የበጎ-ፈቃድ ሠራተኛ (Volunteer) ቡድን፣ ይህም-የሁሉንም ትምህርት ቤቶች የበጎ-ስራ ፈቃድ ሠራተኛን ፕሮግራም ለሚቆጣጠርው ክፍል-መመራት አለበት።

የበጎ-ፈቃድ ሠራተኞች - የሚከተሉትን መረጃዎች በእጃቸው-አድርገት መያዛቸው ጠቃሚ-ሊሆን ይችላል:

የተመደበው ትምህርት ቤት: ______________________________________________

የትምህርት ቤት ስልክ: ______________________________________________

የትምህርት ቤት አድራሻ: ______________________________________________

የአስተማሪ(ዎች)/የተመደበ የትምህርት ቤት ሠራተኛ የመገኛ-አድራሻ(ዎች): __________________

__________________________________________________________

ሌላ የመገኛ-አድራሻ(ዎች):___________________________________________

ርዕሰ-መምህር: ___________________________________________________

የACPS የበጎ-ፈቃድ ሠራተኛ (Volunteer) ቡድን: volunteer@acps.k12.va.us ወይም 571-547-1697
(የበጎ-ፈቃድ ሠራተኛን መዘግየት ወይም መቅረቶች/absencesን ሪፖርት ለማድረግ ጥቅም-ላይ መዋል የለበትም)

## የአሌክሳንድሪያ ከተማ የሕዝብ ትምህርት ቤቶች (ALEXANDRIA CITY PUBLIC SCHOOLS)

### ELEMENTARY AND PREK-8 SCHOOLS

John Adams Elementary School (Grades K-5) 5651 Rayburn Avenue, Alexandria, VA 22311 703-824-6970

Charles Barrett Elementary School (Grades PreK-5) 1115 Martha Custis Drive, Alexandria, VA 22302 703-824-6960

Early Childhood Center (PreK)
5651 Rayburn Avenue, Alexandria, VA 22311 703-578-6822

Ferdinand Day Elementary School (Grades K-5) 1705 N. Beauregard Street, Alexandria, VA 22311 703-619-8430

Patrick Henry Elementary School (Grades PreK-8) 4643 Taney Avenue, Alexandria, VA 22304 : 703-461-4170

Jefferson-Houston School (Grades PreK-8) 1501 Cameron Street, Alexandria, VA 22314 703-706-4400

Cora Kelly School for Math, Science and Technology (Grades PreK-5)
3600 Commonwealth Avenue, Alexandria, VA 22305 703-706-4420

Lyles-Crouch Traditional Academy (Grades K-5) 530 S. St. Asaph Street, Alexandria, VA 22314 703-706-4430

Douglas MacArthur Elementary School (Grades K-5) 1101 Janneys Lane, Alexandria, VA 22302 703-461-4190

George Mason Elementary School (Grades K-5) 2601 Cameron Mills Road, Alexandria, VA 22302 703-706-4470

Naomi L. Brooks Elementary School (Grades K-5) 600 Russell Road, Alexandria, VA 22301 703-706-4440

Mount Vernon Community School (Grades K-5) 2601 Commonwealth Avenue, Alexandria, VA 22305 703-706-44

James K. Polk Elementary School (Grades PreK-5) 5000 Polk Ave., Alexandria, VA 22304 703-461-4180

William Ramsay Elementary School (Grades PreK-5) 5700 Sanger Avenue, Alexandria, VA 22311 703-824-6950

Samuel W. Tucker Elementary School (Grades K-5) 435 Ferdinand Day Drive, Alexandria, VA 22304 703-933-6300

### MIDDLE AND HIGH SCHOOLS

Francis C. Hammond Middle School (Grades 6-8) 4646 Seminary Road, Alexandria, VA 22304 703-461-4100

George Washington Middle School (Grades 6-8) 1005 Mount Vernon Avenue, Alexandria, VA 22301 703-706-4500

Alexandria City High School–Minnie Howard Campus (Grades 9-12)
3801 W. Braddock Road, Alexandria, VA 22302 703-824-6750

Alexandria City High School–King Street Campus (Grades 9-12)
3330 King Street, Alexandria, VA 22302 703-824-6800

Alexandria City High School–Chance for Change Campus (Grades 6-12)
216 South Peyton Street, Alexandria, VA 22314 703-888-1204

Alexandria City High School–Satellite Campus (Grades 9-12)
1340 Braddock Place, Alexandria, VA 22314
703-619-8400

Northern Virginia Juvenile Detention Center School (Grades 6-12)
200 South Whiting Street, Alexandria, VA 22304 703-461-4086

### ACPS VOLUNTEER PROGRAM

Tel: 571-547-1697
www.acps.k12.va.us/volunteer
Volunteer@acps.k12.va.us

VOLUNTEER

*Our Community Cares!*

# የACPS የበጎ-ፈቃድ ሠራተኞች (Volunteers) - እናመሰግናለን!

**ACPS Volunteer Program**

- **Online:** www.acps.k12.va.us/volunteer
- **Email:** Volunteer@acps.k12.va.us
- **Volunteer Phone Line:** 571-547-1697